# ማሃሙድ ጋ ጠብቂኝ!

(መሀመድ ሰልማን)

ስብሓት ‹‹ትኩሳት›› ብሎ በጠራው መጽሐፉ ጀርባ ላይ ምን አለ? “ወጣት ሁን” አለ፡፡ ቢመርህ ‹‹ሪቮሉሽን›› ታስነሳለህ፣ እጅግ ቢመርህ ራስህን ታጠፋለህ…፡፡ ለማንኛውም ወጣት ሁን፡፡ እኔ ግን እልኻለሁ፣ ወጣት መሆኑን ሁን፣ ነገር ግን ራስህን ከማጥፋትህ በፊት ፒያሳ ሂድ፤ ሐሳብህን ልትቀይር ትችላለህና፡፡ ለመሞትም ቢሆን የፒያሳን ያህል መልካም ሰፈር የለም፡፡ ቀባሪ አታጣም፤ በፒያሳ ሰው ባያይህ ማዘጋጃ ያይኻል፡፡ለመሞትም ለመኖርም ስታስብ ፒያሳ ሂድ፡፡



ፒያሳን ለሞትም ቢሆን የምመርጥልህ ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ሞት ሞት የሚሸት ስም በድፍን አዲስ አበባ የምታገኘውም ፒያሳ ነው፡፡ “ዶሮ ማነቂያ” ና “እሪ በከንቱ”ን እንደናሙና ውሰድ፡፡ ‹‹ተረት ሰፈር››ም አንተን ተረት ለማድረግ በሚያስችሉ ሕይወቶች የተሞላ መንደር ነው፤ ተረት መሆን ከፈለግህ፡፡ ፒያሳ ሥጋን ብቻ ሳይሆን ነፍስን ለማጥፋት ጭምር ምርጥ ሰፈር ናት፡፡ ካላመንክ ሙትና ሞክረው፡፡ ነግቶ ሳይመሽ ማዘጋጃ ይቀብርኻል፡፡ ስራ ለማቅለል ከፈለክ ደግሞ እዚያው ማዘጋጃ በር ላይ ጠጋ ብለህ ራስህን መድፋት ትችላለህ፡፡

ፒያሳ ወደ ሕይወትም ልትመልስህ ትችላለች፡፡ “እንዴት?” በለኝ፡፡ ወጣት ነህና ስብሓት በመከረህ መሰረትራስህን የማጥፋት መብትህን ለመጠቀም ወደ ፒያሳ መጣህ እንበል፡፡ የት

ጋር መሞት እንዳለብህ ለመምረጥ በፒያሳ ዞር ዞር ስትል እመነኝ ልብ የምታጠፋ ቆንጆ ታያለህ፡፡ ፀጉሯ የሚዘናፈል፣ ዳሌዋ የሚደንስ፣ ጡቶቿየሚስቁ… መኖር የምታስመኝ ቆንጆ ልቅም ያለች ውብ 13 ቁጥር አውቶብስ ስትጠብቅ ታያታለህ፡፡ በዚህን ጊዜ ልብህ ይሸፍትና አንተም የተፈጥሮ ሞትህን መጠበቅ እንዳለብህ ትረዳለኽ፡፡ ከዚያች ቅፅበት ጀምሮ የ13 ቁጥር አውቶብስ ቋሚ ደንበኛ ሆነህ ታርፈዋለህ፡፡ አውቶብስና ሞት በራሳቸው ሰዓት እስኪመጡ ትጠብቃለህ።

ፒያሳ ወደ ሕይወት መለሰችህ ማለት አይደል?

## የፒያሳ ካፌዎች

ፒያሳ አንድ ሺህ አንድ መቶ ካፌዎች ያሉባት ቅመም የሆነች ሰፈር ናት፡፡ አንድ ሺህ አንድ መቶ ቆንጆ ልጃገረዶች ደግሞ በካፌዎቿ ውስጥ ተኮልኩለው ኮካ በ‹‹ስትሮ›› ይጠጣሉ፡፡ ‹‹ስትሮ›› ምን እንደሆነ ካላወቅክ የፒያሳ ልጅ አይደለህም ማለት ነው፡፡ ‹‹ስትሮ›› በቆንጆ ልጅ ከንፈርና በቆንጆ ብርጭቆ መሀል የተሰራ የላስቲክ ድልድይ ነው፡፡



ፒያሳ በካፌ ብዛት “ከምስራቅ አፍሪካ አንደኛ ናት፡፡” የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ነው እንዲህ ያለው ይባላል፡፡

እንደ ፒያሳ በካፌ የተጥለቀለቀ ሰፈር ከየት ይገኛል?! ከአምፒር እስከ ራስ መኮንን ድልድይ ብቻ በግራና በቀኝ የተሰለፉ ከ53 በላይ ካፌዎችን ልቆጥርልህ እችላለሁ፡፡ በእርግጥ ቆንጆ ልጃገረዶችና ወርቅ ቤቶች በመሀል በመሀል እየገቡ ቆጠራዬን አስተጓጉለዉት ይሆናል፡፡ ሆኖም ቁጥራቸው ከዚህ ቢልቅ እንጂ አያንስም፡፡

የፒያሳ ካፌዎች ልዩ ገፅታ ሁልጊዜ ሙሉ መሆናቸው ነው፡፡ አንዳንድ የፒያሳ ምሁራን ይህንን ጉዳይ

ከመንግሥት የትምህርት ፖሊሲ ጋር ሊያይዙት ይሞክራሉ፡፡ እኔ ግን እላለሁ፤ ይህ የፒያሳ ልዩ ከራማ እንጂሌላ ምንም ሊሆን አይችልም፡፡

በፒያሳ ምርጥ ቡና ጠጥተህ ቀንህን ብሩህ ለማድረግ ካሻህ እነማንኪራ፣ እነ አፍሪካ፣ እነ ቶሞካ አሉልህ…፡፡

ቆንጆ ሻይ ከቆንጆ ልጃገረዶች ጋር ተፋጠህ ፉት ለማለት ካሻህ እነ ናምሩድ፣ እነ ራዜል፣ እነ ኢቪያን፣ እነ ሳሬም፣ እነ ኦስሎ፣ እነ አፕቪው፣ እነ ዲጄስ፣ እነ ሃርድኮር፣ እነ ጉድታይምስ አሉልህ፡፡ በተለይ በቅርቡ የተከፈተው ጉድ ታይምስ እንደ ደብልፌስ ጃኬት አይነት ተፈጥሮ ነበረው፡፡ ቀን ላይ ውብ ካፌ ኾኖ ይቆይና ማታ ላይ በፍጥነት ራሱን ቀይሮ ውብ ባር የመሆን ልዩ ጥበብ ነበረው፡፡ የጨርቆስ ልጆች ያለ ሰፈራቸው መጥተው በቡዳ በሉት መሰለኝ ሰሞኑን ተቃጠለ አሉ፡፡ ነፍስ ይማር!

ፎቅ ላይ ቂብ ብለህ ፒያሳንና ዜጎቿን ቁልቁል እየገረመምካቸው ለመዝናናት ካሻህ አራዳ ላይ የተሰቀሉ መዝናኛዎች አሉልህ፡፡ እነ አራዳ፣ እነ ሲድኒ፣ እነ ትዊንስ፣ እነ ቤስት በፒያሳ ከባህር ጠለል በላይ በምናምን ሺህ ጫማ ከፍታ የሚገኙ ካፌዎች ናቸው፡፡ አለልህ ደግሞ እንደ ዳሎል ተቀብሮ ያለ ካፌ፡፡ ቹንትሮይሰኛል፡፡

ልምከርህ! ፍቅረኛህ ፒዛ አማረኝ ካለችህ ፒያሳ ‹‹ፒዛ ኮርነር›› ውሰዳት፤ ከዚያ በኋላ ምን አለ በለኝ ፍቅሯ ካልጨመረ፡፡ ከዚህ ግብዣ በኋላ ካኮረፈችህ ግን ፒዛውን በልተህባታል ማለት ነው፡፡

ፒያሳ የኬክ አገር ናት፡፡ ዕድሜ ጠገቦቹን ….በዚህ አጋጣሚ ስማቸውን ማውሳት ግድ ይላል፡፡ በተለይ የ‹‹ኤንሪኮ›› ኬክ ይምጣብኝ፡፡ እስኪ በሞቴ ከዚህ ቤት ሂድና ኬክ እዘዝ፡፡ ኪኒን ኪኒን የሚያካክሉ ኬኮች ይቀርቡልኻል፡፡ የፒያሳ ልጅ ካልኾንክ ታኮርፋለህ፡፡ አንተ የለመድከው ድፎ ዳቦ የሚያካክሉ ኬኮችን ነዋ፡፡

እስኪ በሞቴ ቅመሰው፡፡ ከዚያ በአድናቆት ጭንቅላትህን ትወዘውዘዋለህ፡፡ ካልጣመህ ግን በኬክ አላደክም ማለት ነው፡፡ሂድና ሸዋ ዳቦ ተሰለፍ፡፡

ኤንሪኮ ውስጥ ዞር ዞር ብለህ ከጎንህ ያለውን ሰውዬ ገልመጥ ለማድረግ ሞክር፡፡ የሆነ ሰውዬ በትኩረት ኬክ ሲበላ ታየዋለህ፡፡ በእርግጠኝነት ስለሰውየው ብትጠይቅ ከተማዋ ውስጥ ካየኻቸው ሰማይ ጠቀስ ፎቆች የአንዱ ባለቤት ሆኖ ታገኘዋለህ፡፡ ፎቅ ባይኖረው እንኳ ፎቅ የሚሰራ ብር ያለው ለመሆኑ አትጠራጠር፡፡ ይህም ባይኖረው አንድ ቀን የማግኘት ተስፋ

ያለው ነው። የኤንሪኮ የውስጥ ገፅታ አለመብለጭለጭ ተራ ቤት እንደሆነ ሊያስገምትህ ይችላል፡፡ አንድ ነገር ግን ላረጋግጥልህ፣ ይህ ቤት የሞጃዎች መናኸሪያ ነው፡፡ ስለዚህ አትንቀዥቀዥ፡፡



ከኤንሪኮ በኬክ መጋገር ጥበብ ተደንቀህ ስትወጣ ከፊት ለፊትህ የምታገኘው ‹‹እናት ህንፃ››ን ይሆናል፡፡ ይህ ህንጻ በቅርቡ ፒያሳን ከተቀላቀሉ ድንቅ ፎቆች አንዱና ዋንኛው ነው፡፡ በስነ - ህንፃ ታሪክ በምስራቅ አፍሪካ አንደኛ ከመሆኑም በላይ የሚመስለው የለም እየተባለ ነው፡፡ የፒያሳ ልጅ ካልኾንክ ይህን ህንፃ ተደግፈህ ፎቶ ብትነሳና ክፍለ ሀገር ላሉ ዘመዶችህ ብትልክላቸው ልጃችን አሜሪካ ገባ ብለው ድግስ እንደሚደግሱ አትጠራጠር፡፡ አዲስ አበባ ውብ ሕንጻ እንደሌለ የሚያስቡ ዲያስፖራዎችም ቢሆኑ እነሱ በማያውቁት አንድ የአውሮፓ ከተማ ያለ ሊመስላቸው ይችላል። (ካላመንከኝ ፎቶውን ተመልከት)

አይበለውና ፒያሳ ሳለህ ድንገት ስሜትህ ቢመጣ እንደኔ የጨዋ ልጅ ከሆንክ ስልክህን በርበር አድርገህ ትደውልና እጩ ፍቅረኛህን ”ማሃሙድ ጋ ጠብቂኝ” ትላታለህ፡፡ “ኢንተር ላንጋኖ” ወስደህ፣ በድብቆቹ የስሞሽ ግርዶሽ ተጠልለህ፣ ልብ የሚሰልብ የስሞሽ ስነ ስርዓት ትፈፅማለህ፡፡ ከ”ማህሙድ ሙዚቃ ቤት” እስከ “ኢንተር ላንጋኖ” ለመሄድ የሦስት ደቂቃ ትእግስት ካጣኽ ፒያሳ ውላ ትግባ እንጂ ምን ጠፍቶ! በ”አምፒር” ወደ “ዶሮ ማነቂያ” ገባ እንዳልክ “ትሬይን ሀውስ” አለልህ፡፡ ይህ ቤት መሳሳሚያ ብቻ አይደለም ያዘጋጀልህ፡፡

አይበለውና ስሜትህ ከንፈር ብቻ የማያስታግሰው ከሆነብህ ይህ ቤት እጥር ምጥን ያለ ክፍል እጥር ምጥን ላለ ሰዓት ያከራይኻል፡፡ ፒያሳ ነው ያለኸው፡፡ ብታምነኝም ባታምነኝም ፒያሳ ከ10 በላይ መሳሳሚያ ቤቶችን በጉያዋ ይዛለች፡፡ ብዙዎቹ ስም አልባ ናቸው፡፡ ልብህ ከሚቆም አንድ አምስቱን ልጠቁምህ (ሊሞት የመጣን ሰው ወደ ሕይወት ለመመለስ አምስት መሳሳሚያ መቼ አነሰው?)፤ “ኢንተር ላንጋኖ”፣ “ትሬይን ሃውስ”፣ “ቢግትሪ”፣ “ጊቤ”፣ “ቬሮኒካ”…



“ማህሙድ ጋ” ቀጠሮ መያዝ እጅግ የሚመከር እንደሆነ በዚህ አጋጣሚ ሳልነግርህ አላልፍም፡፡ “ለምን?” በለኝ፡፡ አንደኛ ከማህሙድ ሙዚቃ ቤት የሚለቀቁ የማህሙድ ትዝታዎች በቀጠሮ ያስደገፈችህን ልጂትና ያደረሰችብህን ብስጭት የማስታገስ ኀይል አላቸው፡፡ አንዳንዴ ደግሞ የማህሙድ ወዳጅ የነበረው ጥላሁን ‹‹ቀጠሮ ይከበር›› ሲል ያንጎራጎረውን ዜማ ሊከፍቱልህ ይችላሉ፡፡ ሁለተኛ ‹‹ማሃሙድ ጋ›› አስተውለህ ከሆነ ብዙ ቆነጃጅት ብዙ ኮበሌዎችን ቆመው የሚጠብቁበት ስፍራ ነው፡፡ ዕድለኛ ከሆንክ ፍቅረኛዋ ቀርቶባት የተበሳጨችን ልጃገረድ ይዘህ እብስ ልትል ትችላለህ፡፡

ቀጠሮ ቦታ ሴቶች ቢያንስ ሰላሳ ደቂቃ አርፍደው እንደሚገኙ ሳታስተውል አልቀረህም፡፡ ማህሙድ ጋ ግን ለምን እንደሆነ ባላውቅም አረፈዱ ቢባል 20 ደቂቃ ነው፡፡ ቢያረፍዱብህም ከፊት ለፊትህ ብዙ የሚታይና የሚያዘናጋ ነገር አታጣም፡፡ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ትልቁ የሀገራችን የህዝብ ሽንት ቤት የሚገኘው “ማህሙድ ሙዚቃ ቤት” ማዶ ነው፡፡ በቀን ሦስት ሺህ

ሰዎች ይሳለሙታል፡፡ ሽንታቸው እንዳያመልጣቸው የሰጉ አዛውንት ምንትሳቸውን በእጃቸው ደግፈው ወደዚህ ሽንት ቤት እየተወላገዱ ሲገቡ እያየህ መሳቅ ትችላለህ፡፡

ከፈለክ “ሰው የተፈጥሮን ጥሪ ለመመለስ እንደሚጣደፈው ለቀጠሮም ምን አለ ተመሳሳይ ጥድፊያ ቢያሳይ” እያልክ ትፈላሰፋለህ፡፡

ሽንት ያጣደፋቸውን ምእመናን ማየት ከሰለቸህ ቀና በል፡፡ አይንህ ከሕዝብ ሽንት ቤት ወደ ሕዝብ ሶኒክ ስክሪን ይወረወራል፡፡ ፒያሳ በቅርቡ ራሷን ከእህት ከተሞች ጋር ለማስተካከል ያስተከለችው ይህ ትልቅ ዲጂታል ስክሪን የማያሳይህ ነገር የለም፡፡ ከቶሚና ጄሪ አባሮሽ ጀምሮ እስከ ሕገ መንግሥቱ አንቀጾች ይተነትንልኻል፡፡

ሕገ መንግሥቱ የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነት እንዴት እንዳስከበረ ካልገባህ አንቀጽ በአንቀጽ ያስረዳኻል፤

ትንሽ ከቆየህም የሴቶች እኩልነት በአገራችን በአያሌው እየሰፈነ እንደሆነ ያሳይኻል፤ ይሄኔ ከሴት ጓደኛህ ጋር የያዝከው ቀጠሮህ ትዝ ይልኻል፡፡ ሶኒክ ስክሪኑ ላይ በሚታየው የሕገ መንግስቱ አንቀጽ ውስጥ እንዲህ የሚል ነገር እንዲካተትልህ ትመኛለህ፡፡ ‹‹የሴቶች እኩልነት ቀጠሮ በማክበርም ጭምር ይረጋገጥ።››

አይንህን ከሶኒክ ስክሪኑ ስትነቅል የቀጠርካት ልጅ አበባ መስላ ከተፍ ትላለች፡፡ ጉንጮችህን ሳም ሳም፣ እቅፍ እቅፍ ስታደርግህ ንዴትህ ድራሹኑ ይጠፋል፡፡ ጭራሽ ቀጠሮ ማርፈዷ ተዘንግቶህ አንተው ራስህ “አረፈድኩብሽ አይደል” ልትል ይቃጣኻል፡፡ ፒያሳ!

## ክፍል ሁለት

በየትያትር ቤቶች እጅህ እስኪቀጥን ያጨበጨብክለት ድርሰት የተፈጠረው ዶሮ ማነቂያ ውስጥ ሊሆን ይችላል፡፡ የድርሰቱ ቃለ ተውኔት የሚሸመደደውም በእነ “መካ ቤት” የጫት ጉዝጓዝ ላይ ነው፡፡ ደግሞ አርቲስት ብቻ አይምሰልህ የዶሮ ማነቂያን መታወቂያ የወሰደው፡፡ የተማሩና የተመራመሩ፣ ኢትዮጵያ ጨረቃ ላይ ከወጣች መወጣጫ መሰላሉን ያዋቅራሉ የሚባሉ ምሁራን ተራ ሰው መስለው ዶሮ ማነቂያ ይሽሎከሎካሉ፡፡

ማን መሆናቸውን የምታውቀው ግን ከእነርሱ ጋር ለማውራት እድሉ ሲገጥምህ ብቻ ነው፡፡ እውቀታቸው መሬትን ከሰማይ ይደባልቃል፡፡ እነርሱ ግን ከዶሮ ጋር አባሮሽ ይጫወታሉ፡፡

ዶሮ ማነቂያ ሺሻና ጫት ቤቶቿ በየጊዜው በዘመቻ ይታሸጉባታል፡፡ በዚያ ስታልፍ በቤቶቹ በር ላይ በቀይ ቀለም “ታሽጓል” የሚል ጽሑፍም አንብበህ ይሆናል፡፡ ግን እውነት የታሸገ

እንዳይመስልህ፡፡ በጀርባ በኩል መስኮት የሚመስል በር አለው፡፡ የቤቱ ደንበኞቹ ብቻ ናቸው በር መሆኑን የሚያውቁት፡፡ ቀበሌዎችን ለማዝናጋት ዶሮ ማነቂያዎች የፈጠሯት መላ ናት፡፡



### ዶሮ ማነቂያ

በዶሮ ማነቂያ ዶሮ አይታነቅም፡፡ ሰው ግን ይታነቃል፡፡ለምሳሌ ኑሮ አልሞላ ሲለው፤ ወይም ዶሮ እጅግ አምሮት መግዣ ሲያጣ…ኑሮን ቀለል አድርገው መኖር የሚሹ ዜጎች ዶሮ ማነቂያን ይመርጣሉ፡፡ አንተም ኪስህ ቢነጣ፣ መሄጃ ብታጣ ፒያሳ እንደ ቦሌ “ሂድ ከዚህ!” ብላ ውሻ አታደርግህም፡፡ ቦሌ ብዙ ፎርጅድ የቦሌ ልጆች እየተሳቀቁ የሚስቁባት ሰፈር እንደሆነች ልንገርህ፡፡ ፒያሳ ግን 32 ጥርስና 12 ጥርስ ያላቸው ዜጎች እኩል የሚስቁባት ቦታ ናት፡፡ “የቦሌ ልጅ የለውም አባይ” ሲባል ሰምተህ ይሆናል፣ የፒያሳ ልጅ ደግሞ የለውምፎርጅድ፡፡ ድሃና ሀብታም እየተጋፉ የሚዝናኑባት ድንቅ ስፍራ፡፡ ከብሪቲሽ ካውንስል ጀርባ እንደ ፍልፍል ሹልክ እያሉ የሚወጡ ልብን ወከክ የሚያደርጉ ቆነጃጅትን ዐይተህ ይሆናል፡፡ ቤታቸውን ብታየው ትገረማለህ፤ ኩሽና ነው፡፡

ለነገሩ ድፍን አዲስ አበባ ውስጥ ብትዞር ከፎቅ ጀርባ ፎቅ አታገኝም፡፡ በቅርቡ የተወለዱትን ቦሌ መድኀኔዓለምንና አዲሱን ካዛንቺስን ትተህ እግርህ እስኪቀጥን ብትዞር በአዲሳባ ከፎቅ ጀርባ ፎቅ አታገኝም፡፡ካላመንክ እንወራረድ፡፡ ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ የፎቅ ጥቅም በስንት እንደሚከፈል ታውቃለህ? በሁለት ካልክ ትክክል ነህ፡፡ የመጀመርያው የፎቁ ባለቤት ብ…ዙ መስታወት እንዳለው ማስመስከር ሲሆን ሁለተኛውና ዋነኛው ግን ከፎቁ ጀርባ ያለውን ገመና መሸፈን ነው፡፡ ገመና ስልህ የሰፈሩ ወይም የፎቁ ባለቤት ገመና ሊሆን ይችላል።

ይህ ካልገባህ ሂድ ቦሌ፡፡ የአገርህ ቴሌቪዥን የሚኮራባቸው እነ "ሸራተን" እነ "ደምበል"፣ እነ "ጌቱ ኮሜርሻል"፣ እነ "አበሩስ" ጅርባ ማንም ሳያይህ ግባ፡፡ ትበረግጋለህ፡፡ ከዚያን ዕለት ጀምሮ ፎቆችን ታከብራለህ፡፡ ፎቆች ለአገርህ የዋሉት ውለታ እየታሰበህ ዕንባህ በዐይንህ ግጥም ይላል፡፡ "አገሬ ኢትዮጵያ ተራራሽ አየሩ፣ ፏፏቴሽ ይወርዳል በየሸንተረሩ፣ ልምላሜሽ ማማሩ" የሚለው ዘፈን ለምን ፎቆቹን ገሸሽ እንዳረገ አይገባህም፡፡

ቆራጡ መንጌ ፎቅ አልደርስልህ ሲለው አይደል እንዴ ወሎ ሰፈር ሎሊ ህንፃ ፊትለፊት ያሉትን ገመናዎች በግንብ ፕላስተር የጋረዳቸው? መሌ እሳቱ ግን ረጋ ብሎ አሰበ "ችግሩን መቅረፍ ያለብን ከምንጩ ነው" አለ፡፡ ጭርንቁስ ሰፈሮችን ቡልዶዘር ላከባቸው፡፡ የተማረ ይግደለኝ!!

ፒያሳ ፎቅ አልባ ናት፡፡ በእርግጥ የቀድሞው የአገሪቱ ሰማይ ጠቀሱ ሕንጻ "አራዳ" አራዳ ላይ ነው የሚገኘው፡፡

በእርግጥ በጃንሆይ ጊዜ 8 ሚሊዮን ብር የተከሰከሰበት የማዘጋጃ ቤት ሕንጻ ደረቱን ነፍቶ የቆመው በፒያሳ እምብርት ነው፡፡ ግን ፒያሳ ከነቦሌ ጋር ስትነጻጸር ብዙ ፎቆች አሏት ለማለት አያስደፍርም፡፡ ስለዚህ ፒያሳ ብዙ ፎቅ ከሌላቸው የምስራቅ አፍሪካ ሰፈሮች አንዷ ናት ብለን መናገር እንችላለን፡፡

ፒያሳ ፎቅ አልባ ናት ካልን "ገመናዋን ማን ሸፈነላት?" የሚለው ጥያቄ ይከተላል። መልሱ ቀላል ነው፣ ወርቅ ቤቶች፡፡ በፒያሳ ወርቅ ወርቁን ስታይ ከጀርባ ምን እንዳለ ትረሳለህ፡፡ በፒያሳ ቆንጆ ኮረዶች ሽው እልም ሲሉ ስታይ ማሰቢያህ ይሰለባል፡፡ ደፈር ብለህ አንዷን የፒያሳ ቆንጆ ዳሌ ዳሌዋን እያየህ ብትከተላት ግን በብሪትሽ ካውንስል ወይ በአምፒር ወይ በሠራተኛ ሰፈር ቀጭን መንገድ ውስጥ ትገባለች፡፡ መጨረሻዋን ልይ በለህ ትከተላታለህ፤ እስከ ውስጥ፡፡ ድንገት ትሰለብብኻለች፡፡ በዚህ ቅፅበት ምን ሰወራት ብለህ ለራስህ ስታንሾኳሽክ ከጭርንቁስ ቤቷ ወጥታ "ምን አልክ?" ልትልህ ትችላለች፡፡ ስለዚህ የፒያሳ ልጅ አትከተል፡፡ ከተከተልክም እጇን ይዘህ ተከተላት።

ቆንጆ የፒያሳ ልጅ ጠብሰህ ተሳክቶልህ ያውቃል? እንግዲያውስ ልሸኝሽ አትበላት፡፡ ትቀየምኻለች፡፡ "ለምን?" ብለህ ከጠየከኝ ልጅቷ አምልጣሃለች።

ኢትዮጵያዊ ጨዋ፣ ፈሪሐ እግዚአብሔር ያደረበት፣ የሰው የማይመኝ ሕዝብ እንደሆነ ለመመስከር ፒያሳ በቂ ናት፡፡ ፒያሳ የሚገኝን አንድ ቱባ ወርቅ ቤት በህሊናህ አስብ፡፡

ከጀርባው ያለውን ቤትና ቤተሰቡንም ለማስታወስ ሞክር፡፡ ትገረማለህ፡፡ የኋለኛው ቤት ባለቤትና አስራምናምን ልጆቹ ወርቅ ቤቱን ሰርስሮ ስለመግባት አስበው አያውቁመም፡፡ የሸዋ ዳቦ በልተው ሆዳቸውን እያከኩ ወርቅ ቤቱን ተደግፈው ኅብረ-ትርዒት እያዩ ይተኛሉ፡፡

ወርቅ ቤቶችን ከተደገፉ ቤቶች በአመዛኙ የሚገኙት በዶሮ ማነቂያ ነው፡፡ በመሆኑም ለዶሮ ማነቂያ ክብር ስንል ሰፈሩን በዶሮ በረር እንቃኛለን፡፡

ሂድ ዶሮ ማነቂያ፡፡ ውስጥ ውስጡን፡፡ ፒያሳን ፒያሳ ያደረጋት አንዱ ሀብቷ ምን ይመስልሃል? ዶሮ ማነቂያ ነው፡፡ በሃያ ብር 24 ሰዓት ቀብረር ብለህ የምትኖርባት ጉደኛ የፒያሳ ጓዳ፡፡ በቸርነቷ የሚስተካከሏት "አራት ኪሎ ባሻ ወልዴ ሰፈር" እና "አውቶብስ ተራ" ብቻ ናቸው፡፡ እስኪ ለአፍታ የዶሮ ማነቂያን ድርሳን እንግለጥ፡፡

መቼ ለታ ዶሮ ማነቂያ ሄድኩ፡፡ ኪሴ ማፍሰስ ስለጀመረ ሰፈሩን ከሞሉት ማዘር ቤቶች ወደ አንዱ ጎራ አልኩኝ፡፡ ሁሉም የምግብ ዝርዝሮች የቤቱ ግድግዳ እየተፋቀ ተጽፈዋል፡፡ የምግቦቹ ዋጋ ከ10 ብር እንዳይዘል ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ "ጥብስ 9ብር ከ75 ሳንቲም" ይላል፡፡ በዚህ ድንቅ ቤት ድንቅ ምሳ በልቼ ልወጣ ስል እንዲህ የሚል ጽሑፍ ከበሩ የውስጠኛው ክፍል አነበብኩ፡፡ "ቅሬታዎን ለኛ፣ አድናቆትዎን ለጓደኛ!!" በመጨረሻም ተመጋቢዎቹ ከቤቱ ከመውጣታቸው በፊት ከተሰነጣጠቀው የቤቱ ግድግዳ ቀጭን እንጨት ሲመዙ አየሁ፡፡ ስቲኪኒ መሆኑ ነው፡፡ ሲሉ ሰምታ ዶሮ ታንቃ ሞተች!

ሂድ ዶሮ ማነቂያ፤ እነ "መካ ቤት"፣ እነ "ሽመሱ ቤት"፣ እነ "ኑሪያ ቤት"፣ እነ "ቦስ ሺሻ ቤት"፡፡ በቴሌቪዥን ተንሰፍስፈህ የምታያቸው አርቲስቶች አንድ ጥግ ይዘው በነጻነት ሲጋራቸውን ሲያቦኑት፣ በርጫቸውን ቦርጫቸው ላይ አስቀምጠው ሲበርጩት ትመለከታለህ፡፡ ከዚህ ስፍራ ማንም ፈርሙልኝ አይላቸውም፡፡

ማንም አይቁለጨልጭባቸውም፡፡ እነርሱን ከዶሮ አስበልጦ የሚያያቸው ሰው በድፍን ዶሮ ማነቂያ አታገኝም፡፡ ስለዚህ ነጻነታቸውን ለመጎናጸፍ ዶሮ ማነቂያን መረጡ፡፡ እርሷም የነጸነት መሬታቸው ሆነች፡፡

በየትያትር ቤቶች እጅህ እስኪቀጥን ያጨበጨብክለት ድርሰት የተፈጠረው ዶሮ ማነቂያ ውስጥ ሊሆን ይችላል፡፡ የድርሰቱ ቃለ ተውኔት የሚሽመደደውም በእነ "መካ ቤት" የጫት ጉዝጓዝ ላይ ነው፡፡ ደግሞ አርቲስት ብቻ አይምሰልህ የዶሮ ማነቂያን መታወቂያ የወሰደው፡፡ የተማሩና የተመራመሩ፣ ኢትዮጵያ ጨረቃ ላይ ከወጣች መወጣጫ መሰላሉን ያዋቅራሉ የሚባሉ ምሁራን ተራ ሰው መስለው ዶሮ ማነቂያ ይሽሎከሎካሉ፡፡ ማን መሆናቸውን

የምታውቀው ግን ከእነርሱ ጋር ለማውራት እድሉ ሲገጥምህ ብቻ ነው፡፡ እውቀታቸው መሬትን ከሰማይ ይደባልቃል፡፡ እነርሱ ግን ከዶሮ ጋር አባሮሽ ይጫወታሉ፡፡

ዶሮ ማነቂያ ሺሻና ጫት ቤቶቿ በየጊዜው በዘመቻ ይታሸጉባታል፡፡ በዚያ ስታልፍ በቤቶቹ በር ላይ በቀይ ቀለም "ታሽጓል" የሚል ጽሑፍም አንብበህ ይሆናል፡፡ ግን እውነት የታሸገ እንዳይመስልህ፡፡ በጀርባ በኩል መስኮት የሚመስል በር አለው፡፡ የቤቱ ደንበኞቹ ብቻ ናቸው በር መሆኑን የሚያውቁት፡፡ ቀበሌዎችን ለማዘናጋት ዶሮ ማነቂያዎች የፈጠሯት መላ ናት፡፡

ዶሮ ማነቂያ የራሷ መግባቢያም አላት። ለምሳሌ በዶሮ ማነቂያ "ዛሬ የፈረንሳይ ምርጥ ካራቴ ይታያል!" የሚል ማስታወቂያ አንብበህ ይሆናል፡፡ የፒያሳ ልጅ ካልኾንክ ግን ይህ ምን እንደኾነ አይገባህም፡፡ የወሲብ ፊልም ማስታወቅያ ነው፡፡

የሰፈረህ አውራ ዶሮ በቤትህ ጓሮ ሄዶ ሴት ዶሮህ ላይ ቂብ እንደሚለው ሁሉ በዶሮ ማነቂያም ሰዎች እንደዚያ ሲያደርጉ በቴሌቪዥን ታያለህ፡፡ ያለ ምንም ሐፍረት፤ ያውም ሻይ እየተፈላልህ፤ ያውም ለውዝ እየተፈለፈለልህ፡፡ ይህን የሚያሳይህ ቤት የግራና ቀኝ ግድግዳዎቹ በኳስ በምታብድላቸው የአውሮፓ ቡድኖች ፎቶ የተሞላ ነው፡፡ ማዘናጊያ ነው፡፡እግር ኳስ የሚታይ እንዲመስል የተሰቀሉ ናቸው፡፡ በዚህ ቤት ግን እውነት እልኻለሁ ነግቶ እስኪመሽ የአልጋ ጨዋታ ካልኾነ የሜዳ ጨዋታ አይታይም፡፡

በእርግጥ የአልጋ ጨዋታንና የኳስ ጨዋታን እያፈራረቁ የሚያሳዩ ቤቶች በዶሮ ማነቂያ የሉም አልልህም፡፡ ለምሳሌ "አድማሱ ቤት"፣ "ቴዲ ቤት"፣ "ገዛኸኝ ሚስት ቤት" "አንደርግራውንዱ ቤት" ይህንን ያደርጋሉ፡፡ ቀሪዎቹ ግን ለማዘናጊያ ካልሆነ ኳስ ድቡልቡል መሆኗንም የሚያውቁ አይመስለኝም፡፡ በነገራችን ላይ የወሲብ ፊልምን የሚያስኮመኩሙት ቤቶች ቁጥር ከዓመት ዓመት እየተመናመነ መሆኑን ስነግርህ በታላቅ ኀዘን ነው፡፡

ዛሬ አንድ ሰባት የሚሆኑ ጓሮዎች ብቻ ናቸው በድፍን ዶሮ ማነቂያ ወሲብ የሚያስኮሞኩሙት ፡፡ሰዎች የራሳቸውን ፊልም ወደመሥራት አዘንብለዋል ወይም ሌላ ተፎካካሪ ማሳያዎች በአጎራባች ሰፈሮች ተፈጥረዋል ማለት ነው።

በጠቀስኩልህ ቤቶች ግን ልቅ ወሲብ ከማለዳው ሦስት ሰዓት እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰዓት ይታጨዳል፡፡ የጠጅ ቤት አግዳሚ ወንበሮች ተዘርግተው፣ መብራት ጠፍቶ፣ ትንፋሽ ተውጦ፣ ዝምታ ነግሶ ወሲብ ይነግሣል፡፡

የአረብ ወሲብ፣ የህንድ ወሲብ፣ የፈረንሳይ ወሲብ፣ የቻይና ወሲብ፣ የአፍሪካ ወሲብ፣ ሊፍት ውስጥ፣ ጫካ ውስጥ፣ መኪና ውስጥ፣ ኮሪደር ውስጥ፣ ማድቤት ውስጥ፣ ሶፋ ላይ፣ ሼልፍ ላይ፣

ወለል ላይ፣ ደረጃ ላይ፣ በቡድን በተናጥል በተመሳሳይ ፆታ፣ በተቃራኒ ፆታ፣ ከፈረስ ጋር፣ ከሜዳ አህያ ጋር፣ በመጨረሻም ከዶሮ ጋር ይወሰባል፡፡በዶሮ ማነቂያ፡፡ በቴሌቪዥን፡፡

## የዶሮ ስጋና ዶሮ ማነቂያ

ዶሮ ማነቂያ ስድስት ሰዓት ሲሆን በአራራ ታብዳለች፡፡ ድሬዳዋን ታስንቃለች፡፡ ሰዎች ባህርያቸው ይለወጣል፡፡ ይገላምጡኻል፡፡ በዚህ ሰዓት እንደበትህን ለመግራት ሞክር፡፡ በአራራ ጫማ ጥፊ ትመታለህ፡፡ ዶሮ ማነቂያ ቡናን እየተካ ያለውን አረንጓዴ ቅጠላችንን ለፒያሳ ሕዝብ ኤክስፖርት በማድረግ ትራንስፎርሜሽኑን በማፋጠኑ ረገድ የምትጫወተው ሚና የዋዛ አይደለም፡፡ ዶሮ ማነቂያ ጫትን በብዛትና በስፋት ለዜጎቿ በማዳረስ ከሲኒማ ራስ ቀጥሎ በምስራቅ አፍሪካ አንደኛ እንደሆነች በሬዲዮ ሰምቻለሁ፡፡ ያም ሆኖ ከዶሮ ማነቂያ እሴቶች መሀል ወሲብ ቤቶችንና ጫት ቤቶችን ብቻ ዘርዝሮ ይህንን ጽሑፍ መዝጋት የበሉበትን ወጪት መስበር ይሆናል፡፡ በመሆኑም የዶሮ ማነቂያን ድርሳን የምንዘጋው በመልካም ዜና ይሆናል፡፡

የጨርቆስ ልጆች "ከሰፈሮች ሁሉ ማንን ትወዳላችሁ?" ቢባሉ "ዶሮ ማነቂያን አሉ" አሉ፡፡ ለምን ይመስልኻል? በዶሮ ማነቂያ ስጋ እንደተራ ምግብ በየበረንዳው በመስቀያ ተሰቅሎ ስለሚያዩ ነው፡፡ የጨርቆሶችን የሥጋ ፍቅር ደግሞ ያው እንደምታውቀው ነው፡፡ ከራሱ አስበልጦ ሥጋን ይወዳል፡፡ ሥጋን የፈጠረ አምላክ ከፈቀደ "ጨርቆስና ሥጋ" የሚል መጽሐፍ አሳትም ይሆናል፡፡ ማን ያውቃል?

የከተማችን ሥጋ በል ሕዝብ የማያባራ የስጋ አምሮቱን ከሚወጣባቸው ሰፈሮች ውስጥ ከልደታ ቀጥሎ ዶሮ ማነቂያ ትጠቀሳለች፡፡ በጊዮርጊስ በኩል ባለው የዶሮ ማነቂያ "የባህር በር" ያለውን ትእይንት ስትመለከት አዳም የተሳሳተው በበለስ ሳይሆን በሙዳ ሥጋ ሊመስልህ ይችላል፤ የበግ፣ የበሬ እና የፍየል ስጋ እንደጉድ ይነገዳል፡፡

የሚገርመው በዶሮ ማነቂያ የዶሮ ሥጋ አለመገኘቱ ነው፡፡

ገና ወደ ዶሮ ማነቂያ ግዛት አንድ እግርህን እንዳስገባህ ነጭ ጋውን የለበሱ ሥጋ አራጆች ልክ እንደ ጆፌ አሞራ እና ጭልፊት ያንዣብቡኻል፣ ያዋክቡኻል፡፡ ቢላቸውን እያፋጩ፡፡ የፒያሳ ልጅ ካልሆንክ አንተኑ አርደው የሚበሉህ ስለሚመስልህ ትፈራለህ፡፡በነጻ የሚጋብዙህ ይመስል እነርሱ ቤት እንድትገባ ያባብሉኻል፡፡ ቁራጭ ሥጋ አፍህ ውስጥ ወርውረውልህ ኪስህን ሊያራቁቱት እኮ ነው፡፡ እነ "በቀለ" እነ "ባንቡ" እነ "አዱኛ" እነ "ፋሲካ" እነ "ቤተልሄም" እነ "ታደሰ" መስኮታቸውን የሥጋ መጋረጃ አሰርተውለት እንቁልልጭ ይሉኻል፡፡ አይንህ

ሥጋዎቹን በደንብ እንዲያይ ስልሳ ሻማ አምፖል በሥጋው ትይዩ ያበሩልኻል፡፡ የኃይል እጥረት በከተማችን እንዲከሰት ከሚዳርጉ ግዙፍ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ቀጥሎ የሥጋ ቤት አምፖሎች ዋንኛዎቹ ናቸው ብዬ ብጮኽ የሚሰማኝ አጥቻለሁ፡፡

ለማንኛውም እንደ አብዛኛው የአገርህ ዜጋ ሥጋን ለአውድ ዓመት ብቻ የምታገኝ ከሆነ ወይም እንደ ጨርቆስ ልጆች ሥጋን እንደ ኦሎምፒክ በየአራት ዓመቱ የምትበላ ከሆነ በዶሮ ማነቂያ እየተመላለስክ አምሮትህን ልትወጣ ትችላለህ፡፡ "መብላት ነበር!" እያልክ ትዝታለህ፤ ሥጋውን በቅርብ ርቀት እያየህ። ልክ ቅድመ አያቶችህ ጥልያን ላይ እንደፎከሩት፤ አንተም ታቅራራለህ፤ "መብላት ነበር!" እያልክ። በዶሮ ማነቂያ!___

## ክፍል ሦስት

አንተ አገርህ በሁለቱም ቅዱሳን መጽሐፍት መጠቀሷ ልዩ ኩራት እንደሚሰጥህ ሁሉ እኛ የፒያሳ ልጆችም በጸጋዬ ገብረመድኅን ሥራ መካተታችን ያኮራናል፡፡ ‹‹ቦሌ›› የሚለውን ቃል በሰላምታ መጽሔት እንጂ በየትኛውም ቅዱሳን መጻሕፍት አታገኘውም፡፡ ‹‹ጨርቆስ›› የሚለውን ስም በተጨቆኑ ቀልዶች ሲዲ ውስጥ እንጂ የትም አታገኘውም፡፡ ፒያሳን ግን በታላቁ ባለቅኔ ጸጋዬ ገ/መድህን መጽሐፍት እንደልብህ ታገኘዋለህ፡፡



ይህንን ጽሑፍ ስንጀምር እንደብዙዎቹ የጂኦግራፊ ትምህርቶች በ"ዴፊኒሽን" ስላልጀመርኩልህ ይቅርታ እጠይቅኻለሁ፡፡ ፒያሳ የሚለው ቃል የመጣው ከአውሮፓ አህጉር፣ ከጣልያን አገር ሮም ከሚባል ሰፈር ሲሆን ትርጉሙም ‹‹አደባባይ›› ወይም ‹‹ማእከል›› እንደማለት ነው፡፡ ይህ ቃል በአገራችን የትግርኛ ተናጋሪዎች ዘንድም እንደሚታወቅ ስነግርህ በታላቅ ኩራት ነው፡፡ ለምሳሌ ደርባባ ትግሪያዊ እናት ቆንጆ ልጃቸውን ‹‹ኣለይ ማዕረይ

ብፒያሳ አይትኺዲ›› ብለው ቢቆጡ ‹‹ልጄ ማሬ በአስፋልት አትሂጂ›› ለማለት ፈልገው እንደሆነ ትረዳለህ፡፡ ስለሆነም ከእኛው ትግርኛና ከ‹‹ጥልያን›› ባዕድ ቋንቋ ያገኘናቸውን ትርጉሞች በማዳበል ‹‹ፒያሳ›› የሚለው ስርወ ቃል ተፈጠረ፡፡ ትርጉሙን ስንፈታው ደግሞ የሚከተለውን ማለት ሊሆን ይችላል፤ ፒያሳ፤

የቆነጃጅት ማዕከል፣የውቦች አደባባይ፣ ዉበት የሚንዠቀዠቅበት፣ በየአስፋልቱ…በየካፌው!!!




እንግሊዝኛ፣ ጣልያንኛና ህልም እንደፈቺው ነው ይላሉ በጣልያን ጊዜ አርበኛ የነበሩ አበው ሲተርቱ፡፡ እውነት ብለዋል፡፡ ፒያሳ የቆነጃጅት ማርና ወተት ናት፡፡ ካላመንክ ታሪክ አገላብጥ፤ መጻሕፍት ግለጥ፤ አንብብ፤ ጠይቅ። ‹‹እሳት ወይ አበባ››ን አንብበኸዋል? የዛሬ ወጣቶች ከ‹‹ዴርቶጋዳ›› ውጭ መቼ መጽሐፍ ታነባላችሁ?

ለማንኛውም ‹‹ዴርቶጋዳ›› ውስጥ ስሙ የተጠቀሰ አንጋፋ ኢትዮጵያዊ ባለቅኔ አለ፡፡ ስሙም ጸጋዬ ገብረመድኅን ይባላል፡፡ ነፍሱን ይማር፡፡ ከግብሮቹ አንዱ ፍጽም ኢትዮጵያዊ ቅኔዎችን መዝረፍ ነበር፡፡ ‹‹እሳት ወይ አበባ›› አንዱ ቅኔ የዘረፈበት ማሳ ነው፡፡ የሚገርምህ ይህን ድንቅ መጽሐፍ 10 5ኛ ገጽ ላይ ብትገልጠው ይህን ቅኔ ታነባለህ፡፡ ለፒያሳ የተዘረፈ ቅኔ፡፡

አርቀን ማስተዋል ማለት፣ የኛን ስልጣኔ ድልድይ፣
እግር ማየት ነው ብለዋል፣ እስቲ እንግዲህ እግር እንይ፣
ያባቶችህ ያይን ድንበር ከተረከዝ ሎሚ ሳያልፍ፣
አንተ ግን ጆቢራው- ዘራፍ፣
ጠረፍ አይወስንህ ጉብል፣
ጥሎህ በዘመንህ እድል፣
ዓይንህ ባት አልፎ እንዲዋልል፣
ቴይ ወዲያ ጀግንነት የለ፣ ተዚህ የከረረ ግዳጅ፣
ባደባባይ የዱር ገደል፣ስትናደፍ የእግር አዋጅ፣
ሌሊቱን በየሌት‹‹ግለብ››፣ቀኑን ጭምር በጠራራ፣
ሊነጋ እንደ ጧት ጆቢራ፣
በከተማው ስታቅራራ፣
በእድሜህ መንከራተት ስራ፣
– –
እስቲ ደሞ አራዳ ወጥተህ በከተማው አደባባይ፣
ያንዱን ካንዱ ዳሌና ባት፣ እግሯን ከእግር ጋር አስተያይ፣
ደርቶልህ ያገር ልጅ ቅልጥም፣
ዳሌው ባቷ እስኪፈረጥም፣
እያናረ እስኪያገመግም፣
አንተ አድፍጠህ ከኃሏዋ በአይንህ ሳግ ስታነፈንፍ፣
ያችን ልክፍ፣ ያቺን ንድፍ፣
– –
አርቀን ማስተዋል ማለት፣የኛን ስልጣኔ ድልድይ፣
እግር ማየት ነው ብለናል፣ አሜን በቃን እግር እንይ፡፡
ፀጋዬ ገ/መድኅን
ፒያሳ (1983)

አንተ አገርህ በሁለቱም ቅዱሳን መጽሐፍት መጠቀሷ ልዩ ኩራት እንደሚሰጥህ ሁሉ እኛ የፒያሳ ልጆችም በጸጋዬ ገብረመድኅን ሥራ መካተታችን ያኮራናል፡፡ ‹‹ቦሌ›› የሚለውን ቃል

በሰላምታ መጽሔት እንጂ በየትኛውም ቅዱሳን መጻሕፍት አታገኘውም፡፡ ‹‹ጨርቆስ›› የሚለውን ስም በተጨቆኑ ቀልዶች ሲዲ ውስጥ እንጂ የትም አታገኘውም፡፡ ፒያሳን ግን በታላቁ ባለቅኔ ጸጋዬ ገ/መድህን መጽሕፍት እንደልብህ ታገኘዋለህ፡፡

ለማንኛውም ከላይ በቀረበልህ ግጥም በመመስረት የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን መልስ፡፡

1. ግጥሙ ደራሲው የት ቁጭ ብሎ የጻፈው ይመስልኻል?

*ሀ. ጨርቆስ ለ.ፒያሳ ሐ. ቦሌ ድልድይ መ. አሲምባ*

1. ከግጥሙ መንፈስ በመነሳት የ‹‹ቁንጅና ማርና ወተት የሚፈስባት ሰፈር›› የተባለችው?

*ሀ. ላም በረት ለ. ፒያሳ ሐ. ካራቆሬ መ. መልሱን ጸጋዬም ቢሆን አያውቀውም*

ወደዛሬው የፒያሳ ጫወታ ልመልስህ! ፡፡

ፒያሳን ከሌሎች እህት ሰፈሮች ልዩ የሚያደርጋት ለላይኛውም፣ ለታችኛውም የኀብረተሰብ ክፍል የምትመጥን በመሆኗ ነው፡፡ በቀላሉ እንዲገባህ ወጣት ምሳሌ ልስጥህ፡፡ አይበለውና ወንድነትህ አስቸገረህና እንደኔ በጨዋ መንገድ እንደ ጨው የምትጣፍጥ ፍቅረኛህን ‹‹ማህሙድ ጋ ጠብቂኝ›› ብለህ፣ ኬክ ጋብዘህ፣ በጁስ ተለማምጠህ፣ በክትፎ ተለማምነህ ከንፈር ላይ ቂብ ማለት የማትችል ከሆነ፣ አልያም ደግሞ የሴት ቢሮክራሲ ከሰፈርህ ቀበሌ ጋር የሚመሳሰልብህ ከሆነ፣ ፒያሳ መፍትሄ አላት፡፡ እስኪመሽ መታገስ ከቻልክና ኪስህ ድፍን ብሮችን ካቆረ እነ ‹‹ባካል ፀ›› እነ ‹‹ብሉናይል››፣እነ ‹‹ጊቤ›› እነ ‹‹ቼ ጉቬራ›› ይተባበሩኻል፡፡ እስኪመሽ መታገስ ካልቻልክ ደግሞ ‹‹ገሊላ›› የሚባል ቤት አለልህ፡፡ ‹‹ገሊላ›› ቢራ ሳይሆን ማክያቶ አዘህ ከአስተናጋጆቹ ጋር ለ‹‹አጭሬ›› የምትደራደርበት ቤት ነው፡፡ ስለዚህ እና ሌሎች አራት ተመሳሳይ ድብቅ አገልግሎት ስለሚሰጡ እህት ኩባንያዎች በቅርቡ አጫውትህ ይሆናል፡፡

በነገርህ ላይ ‹‹ቼ ኩቬራ›› ለፒያሳ አዲስ ገብ ነው፡፡ ገና ከመምጣቱ የጎረምሶች ቡጢ ቤት ሆኗልኻል፡፡ ይሄ ቤት በጨርቆስ ክፍለከተማ ቢከፈት ይሻል ነበር፡፡ የፒያሳ ልጅ ይመታሃል እንጂ አይደባደብህም፡፡

ዋጋ ከተወደደብህ ደግሞ ቀውጢ ሰፈር ልጠቁምህ፡፡ ከትግራይ ሆቴል እስከ ጣይቱ ሆቴል ያለውን መንገድ ታውቀዋለህ? ይህ አጭር ጎዳና የያዘውን ረዥም ጉድ በዝርዝር ለመግለፅ እንደ መስቀል አደባባይ ሰፊ ብራና ቢገኝም የሚሞከር አይደለም፡፡ በያዘው የሴት አዳሪዎች ብዛት ከምስራቅ አፍሪካ አንደኛ ሳይሆን አይቀርም፣ከአዲሳባ ግን ከቺቺኒያ ቀጥሎ ሁለተኛ

እንደሆነ ስነግርህ ያለጥርጥር ነው፡፡ በዚህ ሰፈር ንጉሳቸውን እንደሚጠብቁ ሚኒስትሮች የመንገዱን ግራና ቀኝ ተሰልፈው የሚቆሙ ልጅ-እግር ኮማሪቶች በየእለቱ ይወለዳሉ፡፡

ደግሞም በየምሽቱ ቁጥራቸው ይጨምራል፡፡ ከየት ነው የሚፈልቁት ልትል ትችላለህ፡፡ ጥሩ ጥያቄ ነው ያነሳኸው፡፡ ሴቶቹ ‹‹አራት ኪሎ››ን፣‹‹አውቶብስ ተራ››ን፣‹‹ጣልያን ሰፈር››ን ከመሰሉ የጎረቤት ቀዬዎች ወደ ፒያሳ ይፈልሳሉ፡፡ ከነዚህ ጎረቤት ሰፈሮች አታለው የሚያመጧቸው ደግሞ እሳት የላሱ የፒያሳ ደላሎችናቸው፡፡ እንዲህ ይሏቸዋል፤ ‹‹ፒያሳ የሚባል አገር አለ፡፤ ወርቅ የሚታፈስበት፤ ባለፀጋ የሚኮንበት፣ፓስፖርት አውጪና ወደ ፒያሳ ልውሰድሽ ለቤተሰቦችሽ ዶላር ትልኪያለሽ፡፡››

ከየሰፈሩ በዚህ መልኩ በደላሎች ለስደት የተዳረጉ ትኩስ ኃይሎች ጣይቱ አካባቢን የስደት መጠለያቸው ያደርጓታል፡፡ ሰራተኛ ሰፈርና ዶሮ ማነቅያ ባሉ ቆጥ ቤቶች አዳራቸውን ያደርጋሉ፡፡

አሁን አሁን እነዚህ የፒያሳ የጎዳና ኮማሪቶች መቆምያ ቦታ እያጡ ስለሆነ ተራ በተራ መተዛዘል ጀምረዋል፡፡

የፒያሳ ክፍለ ከተማ ለነዚህ የጎዳና ኮማሪቶች ወይ ኮንዶሚንየም ቤት ወይ ሴንሴሽን ኮንዶም ወይ መቆምያ ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

ፒያሳን በቅርቡ በምሽት አይተኻት ከሆነ ‹‹ሰንሻይን ባር››፣ ‹‹ገብረትንሳይ ኬክ ቤት››፣ ‹‹መብራት ኃይል ህንፃ››፣ ‹‹ሲኒማ ኢትዮጵያ ደጅ››፣ ‹‹ማህሙድ ጋ››፣ ማህሙድ ቁልቁለቱን፣ ‹‹አራዳ አቀበቱን፣ አላሙዲን አጥሩን ሁሉም ደጆቻቸው በኮልኮሌዎች ተሞልተዋል፡፡ ደፈር ብለህ ከጠየቅክ ኮልኮሌዎቹ ‹‹አውትዶር ሰርቪስ›› ይሰጡኻል፡፡ እየመሸ ሲሄድ ደግሞ ይደፍሩኻል፡፡ ነብሱ፣ ባርዬ፣ባሪቾ፣ቀዮ እያሉ፡፡

በነገርህ ላይ አላሙዲን ላለፉት አስር አመታት ያጠረውን ‹‹የማዘጋጃ ሜዳ›› ሰሞኑን አምርሮ እየቆፈረው እንደሆነ አይቻለሁ፡፡ የቁፋሮዎን ጥልቀትና የወሰደውን ጊዜ በማየት የፒያሳ ጀዝቦች ‹‹ወርቁ ከአዶላ ሳይሆን ከፒያሳ ነው የሚወጣው›› እያሉ ይቀልዳሉ አሉ፡፡ ይህ አላሙዲ ያጠረው ህንፃ ድሮ ወርቅ ወርቅ የእግር ኳስ ተጫዋቾችን ያፈራ ነበር አሉ፡፡ እነ መንግስቱ ወርቁን፤ እነ ወርቁ ኪዳኔን፤ እነ ወርቅነሽ ተስፉን (አራጋቢ ናት)፣ እነ ወርቅነህ ዘውዴን፤ እነ ወርቁ ድንቁን፤ እነ ፍቅሩ ኪዳኔን፡፡

የኢትዮጵያን እግር ኳስ የሚገድለውም የሚያነሳውም አላሙዲን ነው የሚል ፒያሳዊ ፍልስፍና በቅርቡ ሰማሁ፡፡

እንዴት አልኩ፡፡ እንዲህ አሉኝ፤ እሳት የፒያሳ ልጆች፤

‹‹ሼኩ መጫወቻ ሜዳዎችን ለኢንቨስትመንት ይወስድና በምትኩ የውጭ አሰልጣኝ ይቀጥራል፡፡ከዚያ ቡድናችን ጥሩ ይጫወታል ግን የግብ እድል የለውም፡፡ ችግሩ ምንድነው ተብሎ ሲጠና ተጫዋቾቹ ጎል በሌለው ሜዳ ትሬይኒንግ እየሰሩ ነው ተባለ፡፡››

ሼክ አላሙዲ አሰልጣኙን ወስደው ሜዳውን ቢመልሱልን መልካም ሳይሆን አይቀርም፡፡ ባንጫወትም የጎል እድል ይኖረን ነበር፡፡ሼኩ ቶሎ የፒያሳውን ህንፃ ገንብተው ጥሩ ጥሩ ዣንጥላ መሸጫ ሱቅ በመክፈት የስቴድየምን ህዝብ ይክሱታል ብዬ አስባለሁ፡፡ ምስኪን የስቴድየም ሕዝብ፡፡ አሁንም ጎል እየጠበቀ ይዘንብበታል!

ይኸው ስንት ስፖርተኛ ያፈራ የነበረው የፒያሳ ሜዳ አጥሩ ኮልኮሌዎችን አፈራ እልኸለሁ፡፡ ሆኖም ይህ ህንፃ ሲያልቅ ፒያሳ ምን መልክ ይኖራት ይሆን ስል አስባለሁ፡፡ ፈጣሪ ይህን ሳያሳየኝ እንዳይጠራኝ በርትቼ እጸልያለሁ፡፡

የጫወታችንን ውል አሲዞኝማ! ወደ ትግራይ ሆቴል አካባቢ እንመለስ፡፡

ከትግራይ ሆቴል እስከ ጣይቱ ባለው አካባቢው ያሉት ጥቃቅንና አነስተኛ መሸታ ቤቶች ቤት ያፈራቸውን፣ እድል የዞረባቸውን ቆነጃጅት በ‹‹ቴክ አወይ›› እንድትወስዳቸው ዋጋ ያደራድሩኻል፡፡ እነ ‹‹አቢሲኒያ›› በወጣት ላብ ያጥኑኻል፤ እነ ‹‹ኮንቲነንታል››ምራቅ የዋጡ፣ በስራቸው ዶክትሬት የጫኑ፣ ሰፊ የስራ ልምድ ያላቸው ወይዛዝርትን በግዢ ያቀርብልኻል፡፡ ሂድ ደግሞ ‹‹ናሽናል››፣ የአባትህ ታላላቆች ከሴት ጭን የሚወጣ እሳት ሲሞቁ ታገኛቸዋለህ፡፡ የሰፈርህን እድር በሊቀመንበርነት የሚመሩት ሰውዬ የሴት ዳሌ ቸብ ሲያደርጉ ባይንህ በብረቱ ትመለከታለህ፡፡ በነገታው የእድራችሁ ጡሩንባ ለምን በተደጋጋሚ እንደሚነፋ ይገባኻል፡፡

‹‹ትግራይ ሆቴል›› ድሮ ዝነኛ እንጂ ቆንጆ አልነበረም፡፡ እድሜ ለ‹‹አሸባሪዎች›› አሁን ቅልብጭ ያለ ህንፃ ሆኗል፡፡ ከምድር በታች አቀርቅረህ የምትገባበት ዘመናዊ ባር ተከፍቶበታል፡፡ ‹‹ጃምቦ ባር›› ይባላል፡፡ በዘናጭ ባለጌ ወንበሮች እየተሽከረከርክ፣ ዊስኪ ጠርሙሶች ከበው እያስካኩልህ እንደ ልዑል ትጠጣበታለህ፡፡ ከህንፃው አናት ደግሞ ‹‹ቶፕ ቪው›› ካፌ አለልህ፡፡ የፒያሳን አፈር የመሰሉ ጣርያዎች ቁልቁል እያየህ ‹‹አፈር ነኝና ወደ አፈር እመለሳለሁ›› እያልክ ተስፋ ትቆርጥበታለህ፡፡ ለማንኛውም የቀድሞው ትግራይ ሆቴል ከፈነዳ በኋላ እንዲህ አምሮበታል እልኻለሁ፡፡ ሆቴሉ ሰው ተስፋ ካለው ሞቶ መነሳት እንደሚችል የሚያሳይ ህያው ምስክር ነው፡፡ አልዓዛር፡፡

በዚህ የጣይቱ ሰፈር ምን የሌለ ነገር አለ!

ጆሮህ ለሙዚቃ የሰለጠነ ከሆነ፣ በእንግሊዝኛ ማስነጠስ የሚቀናህ ከሆነ፣ የኮማሪቶች ከበርቻቻና ለከት የሌለው ሳቅ የሚያንገሸግሽህ ከሆነ፣ ማንም ባንተ ዛቢያ እንዲሽከረከር የማትሻ ከሆነ፣ ልምከርህ፡፡ ጣይቱ ሆቴልን ተደገፋ የቆመች ትንሽዬ ‹‹ፐብ›› አለች፡፡ ‹‹ፎክላንድ ፐብ›› ትባላለች፡፡ በሙዚቃ ብቻ ስሜትህን አርክተህ፣ ጣጣህን ጨርሰህ፣ የኮንዶም እንኳ ሳታወጣ ወደ ቤትህ ትመለሳለህ፡፡ ወደቤት መሄድ ካልፈለክም ‹‹ፎክላንድ ፐብ›› እስኪነጋ ትታገስኻለች፡፡ በሙዚቃ ፍቅር ያበዱ ዜጎችን ‹‹ሃንግኦቨር›› በሌለው ሙዚቃ የምታሰክር ቀሽት የፒያሳ ፐብ ናት፤ ፎክላንድ፡፡

የሚገርምህ ጣይቱ ሆቴልን ካጀቡት መንግስታዊ ያልሆኑ መጠጥ ቤቶች ሁልጊዜ ፀብና ግርግር አይጠፋም፡፡

‹‹እከሌ እንትትን የገደለው እኮ እዚህ ቤት ነው!›› ትባላለህ፡፡ እድለኛ ከሆንክ ብቻ ነው ከዚህ ቀውጢ ሰፈር ሳትፈነከት የምትወጣው፡፡ በነገርህ ላይ በጣም እድለኛ ከሆንክ ደግሞ በእርምጃ ርቀት ብሔራዊ ሎቶሪ አለልህ፡፡ ቦሌ አካባቢ ቶምቦላ ብታሸንፍ አዝዋሪው ብርህን ዋናው መስሪያ ቤት ሄደህ እንድትወስድ ነው የሚነግርህ፡፡ ፒያሳ ቶምቦላ ቢደርስህ ግን ብርህን እጅ በእጅ መውሰድ ትችላለህ፡፡ከዋናው መስሪያ ቤት፡፡ ጣይቱ ጎን፤ እስኪነጋ ጠብቀህ፡፡

እድለኛ ካልሆክ ደግሞ በፒያሳ በአንደኛው መጠጥ ቤት ከአንድ ጠጪ በተወረወረ ሽራፋ ብርጭቆ ጭንቅላትህን ትተረተራለህ፡፡ ከብሔራዊ ሉቶሪ ፊትለፊት እድለኛ ያልሆኑ ሰዎችን የሚያጉር የአራዳ ክ/ከተማ ፖሊስ ጣብያ አለልህ፡፡ አዳርህ የተጠቀሙበትን ለ‹‹ሽሌ›› አልከፍልም ካሉ ፀረ-ሰላም ኃይሎች ጋር ይሆናል፡፡ ጠዋት የዋስ መብት ተሰጥቶህ አልያም መንግስታችን የይቅርታ ደብዳቤ አስፈርሞህ ወደቤትህ ታመራለህ፡፡

## ክፍል አራት

ፒያሳን የምወድበት ሌላው ምክንያት ባቅላባን ስላስተዋወቀችኝ ነው፡፡(አንዳንዶች ‹‹ቫቅላባ›› ነው የሚባለው ይላሉ፡፡ እኛ ምናገባን፣ ባቅላባውን እንጂ ሆሄያቱን አንበላቸው፡፡)…ይህ የፒያሳ ጭንቅላት ዛሬ ራስ ቅሉ ብቻ ነው ያለው፡፡ በውስጡም ጸረ ሰላም እና ጸረ ልማት የሆኑ እርኩሳን የኤንጂኦ መናፍስትን እያስጮኹ የሚያስወጡ የባህል መድኀኒት አዋቂዎች ተቀምጠውበታል፡፡ ብሪትሽ ካውንስል፣ ነፍስ ይማር!…ፒያሳ

እንዲህ ያወጋሁህን ያህል ብቻ አይደለችም። ምኑን ነካሁትና?! ፒያሳ በሕይወት የተሞላች ብትሆንም ብዙ ሲባልላት ባለመስማትህ ግን ተገርመህ ይሆናል። አትገረም። “ለእነ እንትና ተዘፍኖ ለፒያሳ ሳይዘፈን ይቅር?” ብለህም ይሆናል። አትቆጭ። ምክንያቱ ወዲህ ነው፤ ፒያሳን ለመግለጽ ቋንቋም ወኔ ይጎለዋል። ቋንቋን ራሱን በፒያሳ ሕይወት ተመስጦ

ልታገኘው ትችላለህ። ፒያሳን ለመግለጽ ከመሞከር ይልቅ ፒያሳን መኖር የበለጠ ሐሴት ይሰጣል፤ የስጋም የነፍስም። ይሄው ስንት ዓመታችን ፒያሳን ስንኖራት። የፒያሳ ልጆች ፒያሳን አብረሃቸው እንድትኖር ጋብዘውሃል። ወደ ግብዣው ስትሄድ ግን እስካሁን የሰጠሁህን ምክር በልብህ ያዝ፤ አለበለዚያ የእንትን (የፈለከውን ሰፈርና ከተማ ስም እዚህ ጋ ማስገባት ትችላለህ) ልጅ ነው ብለው ይጥሉሃል።

ፒያሳ፤ ማሃሙድ ጋ እንገናኝ!

ፒያሳ ቅልብጭ ያለች ናት፤ እንደዚህ ጽሑፍ የተንዛዛች እንዳትመስልህ፡፡ “ችቦ አይሞላም” የተዘፈነለት የሴት ወገብ አይተህ ወይንም ነክተህ ወይም ደግሞ አቅፈህ ታውቃለህ? እንደዚያ ማለት ናት ፒያሳ፡፡ ትርፍ ነገር አታይባትም፡፡

የፒያሳ ልጅም ቀልጠፍ ያለ ነው፡፡ አይዝረከረክም፡፡ እንደ ሱሉልታ ልጅ በኮት ላይ ሹራብ አይደርብም፡፡

የዶሮ ማነቅያ ለማኞች እንኳ ሳንቲም ከሰጠኻቸው አይቀበሉህም፤ ወይም ደግሞ አንድ ብር አድርገው ይመልሱልኸል፡፡ ሳንቲም ኮተት ነው፡፡ ፒያሳ አካባቢን የሚያዘወትሩ የታክሲ ወያሎችን አስተውለህ ከሆነ ሳንቲም አይሰጡኹም፡፡ እያጭበረበሩህ እንዳይመስልህ፤ ላንተው ኪስ አዝነው ነው፡፡

ለምን እንደኾነ አላውቅም ሌሎች የአዲሳባ ሰፈሮች እንዲሁ አንዳች ነገር እንደጎደላቸው ይሰማኛል፡፡ ለምሳሌ መርካቶን ውሰድ፤ አፍና አፍንጫው አይታወቅም፡፡ ኮልፌን ውሰድ-ሆድና ጀርባው አይታወቅም፤ ቦሌን ውሰድ-ሴቱና ወንዱ አይታወቅም፤ አራት ኪሎን ውሰድ-ምሁሩና መሀይሙ አይታወቅም፤ ሳሪስን ውሰድ ጫቱና ጫኙ አይለይም፤ ጨርቆስን ውሰድ — በርና መስኮቱ አይለይም፡፡ ፒያሳ ሂድ- ‹‹አሚልቶ አይሰጥ ፈጣሪ›› የሚለውን አገርኛ ቢሂል ከማስታወሻ ደብተርህ ትሰርዛለህ፡፡

ይህንን ጽሑፍ የምጽፍልህ አራዳ ላይ ሆኜ ቁልቁል ‹‹ማህሙድ ሙዚቃ ቤት››ን እያየሁ፣ የፒያሳ ወይዛዝርት ሽው እልም እያሉብኝ፣ ያዘዝኩት ማኪያቶ እየቀዘቀዘብኝ-እያስሞቅኩኝ፣ ብእሬ ቆንጆ ገላን ባየ ቁጥር እየከዳኝ እንደሆነ ልትገነዘብ ይገባል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጽሑፍ ላይ አንዳንድ የቃላትና የሰዋሰው ግድፈት ቢያጋጥምህ ‹‹ቆንጆ ልጅ በ‹‹ማሃሙድ ጋ››አልፋ ነው›› እያልክ እለፈኝ፡፡

ይህ የፒያሳ ወግ እንደረዘመብህ ይሰማኛል፡፡ በነገርህ ላይ ሰፈሮች ለረዘመ ነገር ምላሻቸው ምን እንደሚመስል ታውቃለህ? መርካቶ ወሬ ካረዘምክ ዋጋ ይጨምሩብኻል፤ ቦሌ ወሬ ሲረዝም ራሳቸውን ያማቸዋል፤ ቦሌ መድኀኔዓለም ያጥወለውላቸዋል፤ ጨርቆስ ወሬ ካረዘምክ

‹‹49 ቁጥር ባስ ታመልጥኸለች›› ይሉኻል፤ የአብነት ልጆች ወሬ ካረዘምክባቸው በሹል ድንጋይ መሀል አናትህን ይፈነክቱኸል፤ የፒያሳ ልጆች ወሬ ስታረዝምባቸው ተጨማሪ ኬክ ያዛሉ፡፡ እጅግ ተናደውብኻል ማለት ነው፡፡ ተጨማሪ ኬክ ከማዘዝህ በፊት ይህንን ጫወታዬን እቋጫለሁ፡፡

## የፒያሳ ቤርጎች

መቼ ለታ ማሃሙድ ጋ የመቀጣጠር ጥቅሞቹን ዘርዝሬልህ ሳበቃ፣ የፒያሳን ካፌዎችና ቆንጆ ተስተናጋጆቻቸውን በሚገባ ካስኮመኮምኩህ በኋላ ዶሮ ማነቂያ አስገብቼህ፣ በአላሙዲ አጥር አሻግሬህ፣ ዛሬ ቦታው የኮልኮሌዎች መዋያ እንደሆነ አርድቼህ፣ ጣይቱ ሆቴል አካባቢ አስመሽቼህ ነበር ጫወታዬን የገታሁት፡፡ አስታወስክ?

ዛሬ ትንሽ ጋደም ብለን እናውጋ፤ በፒያሳ ቤርጎዎች፡፡ ለኢትዮጵያ የመጀመርያውን ቤርጎ (በዘመናዊው አጠራር ሆቴል) ያበረከተችው ፒያሳ ናት፡፡ ጣይቱ ሆቴል፡፡ ይህን በልቦናህ ይዘህ ወደ ዝቅተኛ ማደርያዎች ስታማትር ሰራተኛ ሰፈርን ታገኛለህ፡፡

በፒያሳ ማደርያ በሁለት ይከፈላል፡፡ በኮንቦርሳቶና በግድግዳ፡፡ ለምሳሌ በዶሮ ማነቅያና በሰራተኛ ሰፈር ያሉ ማደርያዎች ዋጋቸው ከሀያ እስከ 40 ብር ሲሆን ከቀጣዩ ጎረቤትህ የሚለይህ ግን ኮምቦልሳቶ የሚባል ቀላል "ቴክኖሎጂ" ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ከጎንህ ያለውን የቤርጎ ተከራይ ገመናዎችና በእንቅልፍ ልቡ የሚጫወታቸውን ቀላል የትንፋሽ መሳርያዎች ለመስማት ትገደዳለህ፡፡ ጫን ያለው የሚያንኮራፋ ቤርጎ ተከራይ ሲመጣ ደግሞ የምትሰማው ሙዚቃ ወደ ጃዝ ከፍ ይላል፡፡ ከሁሉም የከፋው ግን ጎረቤትህ ሴት ይዞ የገባ ከሆነ ነው፡፡ በዚህን ጊዜ የሚሰማህ ሙዚቃ የጣልያን ኦፔራ በኦርኬስትራ ታጅቦ ሊሆን ይችላል፡፡

ሠራተኛ ሰፈር በቤርጎ ብቻ ሳይሆን በሕጻናትና ወጣቶችም እየተጥለቀለቀ ነው፡፡ በሰፈሩ ያለውን የሕጻናት ብዛት ስታይ የዚህ ሰፈር አባቶች እና እናቶች ማታ ማታ ምን ያህል ጠንክረው እንደሚሠሩ ይገባኻል፡፡ የትኛው ልጅ የየትኛው ቤት አባል እንደሆነ የሚለየው በሚያሰማው የአለቃቀስ አይነት ነው እየተባለ ይቀለዳል፡፡

የሠራተኛ ሰፈር አባወራዎችና እማወራዎች እነዚህን ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ሕጻናት ለማሳደግ ታድያ ለፒያሳ የውድቅት ሰለባዎች አልጋ ያከራያሉ፡፡ ችግሩ አልጋ ተከራይ ሲጠፋ በዚያው በሚከራይ አልጋ ላይ ሌላ ልጅ ሠርተው ያድራሉ፡፡ ሠራተኛ ሰፈር!!!

ፒያሳ መካከለኛና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቱሪስቶች አልጋዎችን ታከራያለች፡፡ ‹‹እቴጌ ጣይቱ››እና ባለቤታቸው ከዓመታት በፊት ያባረሯቸው ፈረንጆች የ‹‹እቴጌ ጣይቱ››ን ረከስ ያለ

አልጋ ፍለጋ ዳግም ፒያሳን አጥለቅልቀዋታል፡፡ ፒያሳ ጥልያን በጣልያን ሆናለች፡፡ በፒያሳ ከምትገምተው በላይ ፀጉረ ልውጥ በዝቷል፡፡

ለፒያሳ ጩሉሌዎችም አዲስ የሥራ እድል ተፈጥሯል፡፡ ጣይቱ ማዶ ያሉ ሰፈሮች በሙሉ ወደ ኢንተርኔት ካፌ የተለወጡት ወደው አይምሰልህ፡፡ ፈረንጅ በዝቶ ነው፡፡ ከሰሞኑ አንድ አባት አርበኛ በዚያ ጋር አልፈው ምን አሉ መሰለህ፡፡ ‹‹ጥልያንን አባረነው አልነበረም እንዴ?!››

‹‹ዉጥማ ሆቴል››፣ ‹‹ባሮ መኝታ››፣ ‹‹አንኮበር እንግዳ ማረፍያ›› ሁሉም ከጣይቱ ጀርባ የሚገኙ ፈረንጅ ተኮር መኝታ ቤቶች ናቸው፡፡ አንተም እገባለሁ ካልክ ቆዳህን ማድማት አይጠበቅብህም፡፡ ኪስህን እንጂ፡፡

## የፒያሳ ጣእም

ፒያሳን በካፌዎቿ እንጂ በምግብ ቤቶቿ የሚያውቃት ሕዝብ እምብዛም ነው፡፡ ይህ ግን ድንቁርና ድህነት ያመጣው ጣጣ እንጂ የፒያሳ ችግር አይደለም፡፡ እመነኝ፡፡ በከተማችን ትልቁ፣ ዝነኛውና ውዱና ተወዳጁ ምግብ ቤት የሚገኘው በፒያሳ እንደሆነ የፒያሳ ልጆችም አንዳንዴ ይዘነጉታል፡፡ የከተማችን ዲፕሎማቶች፣ ባለሀብቶች፣ ባለሚሎች ዘናጭ ምግብ መብላት ሲሹ የት የሚሄዱ ይመስልኻል፡፡ ቦሌ እንዳትለኝና እንዳልስቅ፡፡

ፒያሳ ነው የሚመጡት፡፡ ካስቴሊ፡፡

ካስቴሊን ጥቂት ሰው ነው የሚያውቀው፡፡ ምግብ ቤቱ በተፈጥሮው ድምፁን አጥፍቶ ነው የሚሰራው፡፡ ስታየው ምግብ ቤትም አይመስል፡፡ ከማህሙድ ሙዚቃ ቤት በስተቀኝ አምስት እርምጃ አይርቅም፡፡ ካስቴሊ እንደማንኛውም ምግብ ቤት መስሎህ ዘለህ ዘው እንዳትል፡፡ ለነገሩ ዘበኛው ወዝህን አይቶም ቢሆን ይከተልኻል፡፡ የዚህ ቤት ዘበኞች ‹‹ሽሮ-በል››ና ‹‹ስጋ-በል›› ዜጎችን በፍጥነት እንዲለዩ ተደርገው የተገሩ ናቸው፡፡

እዚህ ቤት መብላት ካማረህ ብዙውን ጊዜ አስቀድመህ በስልክ ቦታ አሲዘህ ነው መሄድ ያለብህ፡፡ ደግሞ ተኳኩለህ፣ ዘንጠህ ብትሄድ ይመከራል፡፡ አልያ እጅህን ልጥታጠብ ስትነሳ ተስተናጋጆች አስተናጋጅ መስለሃቸው ‹‹ሂሌ !ማነህ! እዚህ ጋ እስኪ የዳቦ ክሬም ጨምር›› ይሉኻል፡፡ በዚህን ጊዜ ከፍተኛ የሞራል ኪሳራ ደርሶብህ በልቼ እወፍራለሁ ያልከው ሰውዬ ከስተህ ትመለሳለህ፡፡

ዘወትር ምሳ ሰዓት ላይ ‹‹ቪ ኤይት››፣‹‹ፌራሪ››፣‹‹ሀመር››፣‹‹ኤስካሌድ››፣‹‹ኤክስ ፋይቭ››፣ ‹‹ሬንጅሮቨር››፣‹‹ኢንፊኒቲ›› የመሳሰሉ የሚሊዮን ብር መኪናዎች በካስቴሊ ምግብ ቤት በር ላይ እንደቀልድ ተሰድረው ታያለህ፡፡ ጠርጣሪ ከሆንክ ደግሞ ትጠረጥራለህ፡፡ አንዳች ባለጸጋ የፒያሳን ምድር ረግጧል ስትል፡፡

አልተሳሳትክም፡፡ በካስቴሊ መናኛ ሰው አይገባም፣አይበላም፡፡ ደጅ የቆሙ መኪናዎችን ግን እንዲጠብቅ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡ ከዚህ ቤት በር መኪና ጠብቀህ የሚሰጥህ ‹‹ቲፕ›› ዶሮ ማነቅያ ውስጥ ምን የመሰለ ቅቅል ታዝበታለህ፡፡

የምትወዳት ፍቅረኛ ካለችህ ግን ምን ታደርግ መሰለህ፤ ከየትም እንዴትም ብለህ ብር አጠራቅም፡፡ ፒያሳ ማህሙድ ጋ ቅጠራት፡፡ ፒያሳ ካስቴሊ ምሳ ጋብዛት፡፡ ምን አለ በለኝ ትጋባላችሁ፡፡

## የፒያሳ ቡቲኮች

የሆነ ሰፈር ልብስ ልትገዛ ገብተህ ይሆናል፡፡ ሻጩ እንዲህ ይልኻል፡፡ *‹‹አባዬ፤ ይሄን ጃኬት ፒያሳ 800 መቶ ብር ይሉኻል፡፡ እኛ ላንተ ብለን ነው…ባገር ዋጋ ልበሰው…ትከሻ አለህ፤ ሂዶብኻል! (አንተ የትከሻህን ገለባነት ስለምታውቀው ሳቅህ ይመጣል) አታውልቀው ያምርብኻል! እኔ ለናቴ ልጅ አልሸጠው…!!! ምትገዛበትን ንገረኝና እንስማማ…››*

ፒያሳ ዋጋ ይቆለላል፡፡ ሌላ ቦታ 300 ብር የምትገዛውን ልብስ ፒያሳ እጥፉን ትጠይቅኻለች፡፡ ለውድ አፈሯ ግብር መሆኑ ነው፡፡ ምናለ ብትከፍል?! "ከፒያሳ ነው የገዛሁት" ስትላት ሴት ጓደኛህ ትመካብኻለች፡፡ እመነኝ፡፡ ከዚያ በኋላ "መች ነው የምንጋባው?" ትልህ ይሆናል፡፡ ልብስ ጫማ ከገዛህ ከፒያሳ ግዛ፡፡ ዝናህ ለጉረቤት ይተርፋል፡፡ የጨርቆስ ልጅ ከሆንክ ደግሞ ዝናህ በሰፈሩ ይናኛል፤ ኪሎ ስጋ የገዛህ ይመስል፡፡

## ሲኒማ ላ ፒያሳ

ስማኝማ! ኢትዮጵያ ውስጥ ሲኒማ የት እንደተጀመረ ታውቃለህ? ፒያሳ ነው፡፡ ካላመንክ ሂድ ቴዎድሮስ አደባባይ፡፡ ‹‹ሰባስቶፖል›› አፍንጫውን ወደቀሰረበት አቅጣጫ ተመልከት፡፡ ሰይጣን ቤትን ወይም ሸይጣን ቤትን ታገኛለህ፡፡ ካላመንከኝ የታሪክ መጻሕፍትን ፈትሽ፡፡ እኔ የነገርኩህን ይደግሙልኻል፡፡ በዚህ ቦታ ‹‹ዋልታ›› ረዥም ፎቅ ሊሰራበት ነው፡፡ ፎቅ ሳይቆምበት ቶሎ እየው፡፡ ታድያ ስትገባ አማትበህ፣ አልያም ‹‹ቢስሚላህ፣አኡዙ ቢላህ›› ብለህ ግባ፡፡ ሰይጣን ቤት መሆኑን አትርሳ፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ በጣት የሚቆጠሩ ሲኒማ ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ከ 85 በመቶ በላይ የሚገኙት በፒያሳ እንደሆነ ማን በነገረህ፡፡ ፒያሳ የኢትዮጵያ ሆሊውድ ልትላት ትችላለህ፡፡‹‹ሰይጣን ቤት››፣‹‹ሲኒማ ኢትየጵያ››፣ ‹‹ማዘጋጃ ቤት››፣ ‹‹አገር ፍቅር››፣‹‹ሲኒማ አምፒር››፣ ‹‹እስክስታው ቤት››፣ እንዲሁም አገር በቀል የዶሮ ማነቅያ ቪዲዮ ቤቶች ወዘተ ሁሉም ፒያሳ ነው ቤታቸው፡፡

ድሮ ‹‹ሲኒማ ኢትዮጵያ›› አልሳም ያለችህን ፍቅረኛ ወስደህ በፊልም አሳበህ የከንፈር ዳር ድንበሯን

የምትጋፋበት ቤት ነበር፡፡ ሆኖም እጣህ ሆኖ ሴት ጓደኛህን ይዘህ የገባህ እለት የህንድ ፊልም ከከፈቱብህ አለቀልህ፡፡ ጓደኛህ ከህንዶቹ እያየች አልሳም ትልኸለች፡፡ ለማፏጨትም ለመሳምም ያልተመቸ ሲኒማ ምኑን ሲኒማ ነው?!

እኔም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይኸው ‹‹ሲኒማ ኢትዮጵያ›› የምሄደው ከደጁ የሚሸጡትን የእንግሊዝኛ መጽሔቶች ለመግዛት ብቻ ሆነ፡፡ ጊዜው እንዴት ይሮጣል?

## የባቅላባ ፍቅር

ፒያሳን የምወድበት ሌላው ምክንያት ባቅላባን ስላስተዋወቀችኝ ነው፡፡(አንዳንዶች ‹‹ቫቅላባ›› ነው የሚባለው ይላሉ፡፡ እኛ ምናገባን፣ ባቅላባውን እንጂ ሆሂያቱን አንበላቸው፡፡)

ትዝታ ገብረትንሳኤ ወመኮንን ባር፡፡

“መኮንን ባር” የፒያሳ አድባር ነው፡፡ ይህ ቤት የማን ነው? የሕዝብ ይመስለኛል፡፡ ባለቤቱን አይቼው አላውቅም፡፡ ደግሞ ባለቤት ያለውም አይመስለኝም፡፡ እንዴት በእኔ እድሜ እንኳ አይታደስም? እነዚያ በሕጻናት መዋያ ትምህርት ቤቶች ያሉትን ወንበሮች የሚመስሉ ትንንሽ ቡናማ መቀመጫዎች፣ ባቅላባ ከሚያካክሉ ትንንሽ ጠረጴዛዎች ጋር አሁንም አሉ፡፡ እንደነበሩት፡፡ ወደፊትም የሚኖሩ ይመስለኛል፤ ከማይደበዝዘው ግርማ ሞገሳቸው ጋር፡፡

አንጀቴን የሚበሉ አስተናጋጆች ያሉበት ቤት ነው፤ መኮንን ባር፡፡ ከቤቱ ጋር ያረጁ፣ ያጎነበሱ ውድ አስተናጋጆች፡፡ ቲፕ ባልተለመደበት ዘመን ሥራ ጀምረው እንጂ እስከዛሬ እነርሱም ባለ ባር በሆኑ ነበር እላለሁ፤ በሆዴ፡፡ ለማንኛውም ለረዥም ዓመት ስላስተናገዳችሁኝ እጅ እነሳለሁ፡፡ ከልቤ፡፡

ባቅላባ ቤት የወንበርን ጥቅም ያወቅኩበት ቤት ነው፡፡ ወንበር ከያዝክ የሚታዘዝህ ይመጣል፡፡ ውሀ ይቀርብልኻል፤ ባቅላባህ ይመጣልኻል፤ ስትጨርስ ጠረጴዛህ ይጸዳልኻል፡፡ ወንበር ከሌለህ ግን ሄደህ፣ተሰልፈህ፣ ከፍለህ፣ ባቅላባ ለመውሰድ ሌላ ሰልፍ ይዘህ፣ ሹካና ማንኪያ ለማግኘት ደግሞ ሌላ ሰልፍ ይዘህ፣ ውሃ ለማምጣት ደግሞ ሌላ ሰልፍ ጠብቀህ፣ ሰርተህ ትበላለህ፡፡ ወንበር ጥሩ ነው፡፡ ግን ደግሞ ለቀጣይ ትውልድ መልቀቅም ይገባል፡፡ አገኘኹ ብለህ 20 ዓመት በባቅላባ ወንበር ላይ መወዘፍ የለብህም፡፡ ይህች ዓረፍተ ነገር ፖለቲካ መሰለችብኝ ልበል? ግን ንጹሕ ነገረ ባቅላባ ናት።

ባቅላባ ዛሬም አለ፡፡ እስከ ስምንተኛው ሺህ ይኖራል፡፡ ዋጋው ስምንት ብር ደርሷል፡፡ ሰልፉም እንደዚያው፡፡ ሌላ ትውልድ በተራው እየበላው ነው፡፡ በእነዚያው አስተናጋጆች፡፡

## ዳላስ ሙዚቃ ቤት

ፍቅረኛህን ‹‹ማሃሙድ ጋር ጠብቂኝ›› ስትላት ተሳስታ ተሻግራ ከጠበቀችህ እድለኛ ናት፡፡ ካንተ በላይ የሚያስደስቷትን ሙዚቃዎች እየሰማች ነው ማለት ነው፡፡ ከዳላስ ሙዚቃ ቤት፡፡ ይህ ቤት የየመን ዝርያ ባላቸው ሐበሾች የተያዘ ነው፡፡ ከፒያሳ ፍቅር እንዲይዝህ ከሚያስችሉ አዚሞች አንዱ ነው፤ ዳላስ፡፡

እጅግ የቆዩ የሚጣፍጡ ሙዚቃዎችን ዛሬም ድረስ ያስኮመኩማል፡፡ ከዚህ ቤት የሚደመጡ ሙዚቃዎች ዘፋኞቹ በህይወት የሌሉ ወይም ደግሞ ዘፋኞቹ ራሳቸው የረሷቸው ሙዚቃዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ‹‹ኦልዲስ-በት- ጉዲስ››፡፡

አንድ አንባቢዬ ዳላስን እንዴት ገለጸው መሰለህ፤ ‹‹The soundtrack of Piassa››፡፡

ዘላለማዊ የሆኑ ዘመን የማይሽራቸው የሱዳንና የአገረሰብ ሙዚቃዎች በዚህ ቤት ይዘወተራሉ፡፡ በቲቪ የምታውቀው ጀማሪ ዘፋኝ እዚህ ዳላስ ሙዚቃ ቤት አካባቢ ሲያንዣብብ ካየኸው አንድ ነገር ጠርጥር፡፡ ሊከትፍ ወይ ሊመነትፍ ነው፡፡

## የፒያሳ ጭንቅላት

የፒያሳ ሆድ ካስቴሊ ነው። የፒያሳ ሀብት ወርቅ ቤቶቿ ናቸው፡፡ የፒያሳ ጆሮ ዳላስ ነው፤ የፒያሳ አይን ሲኒማ አምፒር ነው፤ የፒያሳ መልክ ውብ ሴቶቿ ናቸው፡፡ የፒያሳ ራስ ቅል ማዘጋጃ ቤት ነው፡፡ የፒያሳ ጭንቅላት ማን ነው?

ወዳጄ ኸይ! በፒያሳ ውብ ጫማና ልብስ ብትሽቀረቀር፣ ካስቴሊ ሄደህ ከርስህን ብትሞላ፣ አምፒር ሴት ሸጉጠህ ኋላ ወንበር ላይ ብትወሸቅ፣ ፒሳ ኮርነር ብትነጠፍ፣ በባቅላባ ጣእም እጅህን ብትቆረጥም፣ በኤንሪኮ ኬክ ብትንሳፈፍ፣ ማህሙድ ጋ ልጅቱን ጥበቃ በጭንቅላትህ ብትተከል፣ በዳላስ ሙዚቃ ብትመሰጥ፣ በሰንሻይን ሻምፓኝ ብትራጭ፣ የዶሮ ማነቂያን ቁርጥ ብትዘነጥል፣ ጭንቅላት ባዶ ከሆነ ምን ዋጋ አለው? ጭንቅላትም ልክ እንደሆድህ ምግብ እንደሚፈልግ ታውቃለህ። ለዚህ ፒያሳ ብሪትሽ ካውንስል አለልህ፤ ነበረልህ፡፡ ዛሬ ስልጣን መሰይጠን ነው ብለው በስደት ሆነው አገርህን በእውቀት ከሚያሾፉት ኢትዮጵያውያን የሚበዙት ጭንቅላታቸውን የት የኮተኮቱት ይመስልኻል? በብሪትሽ ካውንስል ቤተ መጻሕፍት ነው፡፡ ብሪትሽ ካውንስል ደግሞ የፒያሳ የእውቀት አድባር ነው፡፡ የዚህን ቤት ውለታ የምታውቀው እውቀት ጠገብ ከሆኑ ሰዎች ጋር በፒያሳ ካፌዎች በአንዱ ቁጭ ብለህ የማውጋት

እድል ከገጠመህ ነው፡፡ ብሪትሽ ካውንስል ዓለምን አሳይቷቸዋል፡፡ ጭንቅላታቸውን ትራንስፎርም አድርጎላቸዋል፡፡ የጭንቅላታቸው ትራንስፎርመር እንዳይቃጠል ረድቷቸዋል፡፡ ገና ድሮ፤ የትራንስፎርሜሽንና የምናምን እቅድ ሳይጠነሰስ፡፡ ጠንሳሾቹም ሳይጠነሰሱ፤ ሳይጠነስሱም፡፡

በዚህ ቤት ኢትዮጵያውያን በሼክስፒርኛ ተቀኝተዋል፣ በፕላቶኛ ተፈላስፈዋል፣በመጻሕፍት ባህር ተንቦራጭቀዋል፡፡ በየምእራብ አገራቱ ፈረንጅ ያቃተውን ሳይንስ የሚፈትሉት እኒህ ጥቂት ኢትጵያውያን የብሪትሽ ካውንስል ቡቃያዎች ናቸው፤ የብሪትሽ ካውንስል ውለታም አለባቸው፡፡ አፋቸው በእንግሊዝ አፍ ለማሰልጠን መሂጃ ያጡ ብቅ የሚሉት እዚህ ነበር፤ ለልጆቻቸው መጻሕፍት የሚዋሱ ወላጆችን ማየት ብርቅ በነበረበት ዘመን በብሪቲሽ ካውንስል በሽ ነበሩልህ። ለማትሪክ ዘመቻ የሚዘጋጁ ጮሌዎችም ለንባብ ሲንጋጉ ታያቸው ነበር።

ምን ዋጋ አለው ታድያ፡፡ ይህ የፒያሳ ጭንቅላት ዛሬ ራስ ቅሉ ብቻ ነው ያለው፡፡ በውስጡም ጸረ ሰላም እና ጸረ ልማት የሆኑ እርኩሳን የኤንጂኦ መናፍስትን እያስጮኹ የሚያስወጡ የባህል መድኀኒት አዋቂዎች ተቀምጠውበታል፡፡ ብሪትሽ ካውንስል፣ ነፍስ ይማር!

## ማሰርያ አንቀጽ

ፒያሳ እንዲህ ያወጋሁህን ያህል ብቻ አይደለችም። ምኑን ነካሁትና?! ፒያሳ በሕይወት የተሞላች ብትሆንም ብዙ ሲባልላት ባለመስማትህ ግን ተገርመህ ይሆናል። አትገረም። “ለእነ እንትና ተዘፍኖ ለፒያሳ ሳይዘፈን ይቅር?” ብለህም ይሆናል። አትቆጭ። ምክንያቱ ወዲህ ነው፤ ፒያሳን ለመግለጽ ቋንቋም ወኔ ይጎለዋል። ቋንቋን ራሱን በፒያሳ ሕይወት ተመስጦ ልታገኘው ትችላለህ። ፒያሳን ለመግለጽ ከመሞከር ይልቅ ፒያሳን መኖር የበለጠ ሐሴት ይሰጣል፤ የስጋም የነፍስም። ይሄው ስንት ዓመታችን ፒያሳን ስንኖራት። የፒያሳ ልጆች ፒያሳን አብረሃቸው እንድትኖር ጋብዘውሃል። ወደ ግብዣው ስትሄድ ግን እስካሁን የሰጠሁህን ምክር በልብህ ያዝ፤

አለበለዚያ የእንትን (የፈለከውን ሰፈርና ከተማ ስም እዚህ ጋ ማስገባት ትችላለህ) ልጅ ነው ብለው ይጥሉሃል።

**ፒያሳ፤ ማሃሙድ ጋ እንገናኝ።**

**ተፈጸመ።___**